# ወርሓዊ ዜና ሚቲዎሮሎጂ

# Monthly Met. News







የአይሪሽ ኤይድ ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ወርክሾፕ ተሳታፊዎች በደቡብና በትግራይ ክልል

## ቅጽ 4 ቁጥር 6 የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት

ታኅሳስ 2010 ዓ.ም

# የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ በሄክታር ቢያንስ ለ10 ኩንታል የምርት ዕድገት ምክንያት ሊሆን እንደሚችል በተመራማሪዎች ተረጋገጠ፣

"ምንም ያህል ምርጥ ዘር ቢቀርብ፣ ምንም ያህል ቶን ማዳበሪያ ብንጠቀም ግብርናችን በአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ካልታገዘ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥም ሆነ ምርታማነትን ማሳደግ አይታሰብም"

*የዘርፉ ተመራማሪዎች እ.ኤ.አ ከ25-26/2017 ዲሴንበር በአይሪሽ ኤይድ ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ወርክሾፕ ላይ ከተናገሩት*

ተመራማሪዎቹ የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ትንበያዎችን በመጠቀምና ባለመጠቀም መካከል በምርት እድገት የሚኖረውን ልዩነት ያረጋጡት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በብዛት ለዝናብ እጥረትና ድርቅ ተጋላጭ የሆኑ ሦስት ወረዳዎች ማለትም ቦሪቻ፣ ሼበዲኖ እና ሀላባ ለጥናታቸው የመረጡ መሆናቸውን አሳውቀዋል፡፡ ከነዚህም ወረዳዎች 50 የአርሶ አደር ማሳዎችን ለጥናት የመረጡ ሲሆን 25 ማሳዎች ለምርምር የተጠቀሙ መሆኑን ማለትም ተመሳሳይ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ እንዲሁም የአፈር አይነትን ጨምሮ በመመርመር በሃምሳዎቹ ማሳዎች ላይ ተመሳሳይ መሆናቸውን በማረጋገጥ እና የሚቲዎሮሎጂ ትንበያን ለ25ቱ በመስጠትና ለ25 ባለመስጠት ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አጨዳው ድረስ የሚስተዋሉ ልዩነቶችን በቅርበት በመከታተል ያጠኑትን ጥናትና የደረሱበትን ድምዳሜ ለውይይቱ ተሳታፊዎች በፎቶ ጭምር አቅርበዋል፡፡

ይህ የምርምር ውጤት የቀረበው ከ65 በላይ አርሶ-አደሮች፣ የልማት ሠራተኞች፣ የክልሉና ከየወረዳው የመጡ የግብርና ጽ/ቤትና ቢሮ ኃላፊዎች በተገኙበት በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት በሁለተኛው ዙር ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ከዓለም የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ጋር በመተባበር ከአይርላንድ መንግስት ባገኘው ድጋፍ ተግባራዊ ሲደረግ በነበረው ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ፕሮግራም ላይ መሆኑም ታውቋል፡፡

ከአይርላንድ መንግስት (አይሪሽ) በተገኘው ድጋፍም ብሔራዊ የሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ለሀምሳውም አርሶ-አደር ተመሳሳይ ምርጥ ዘርና ማዳበሪያ በማቅረብ እንዲሁም ከፕላስቲክ የተሰራውን የዝናብ መጠን መለኪያ (ሬንጌጅ) በማቅረብና በአርሶ-አደሩ ማሳ ውስጥ በሚተከልበትና የዝናብ መጠኑ በሚለካበት አግባብ ላይ በባለሞያዎች ስልጠና በመሰጠት ወደ ተግባር መገባቱን ተመራማሪዎቹ አሳውቀዋል፡፡

ከዚህ በተጨማሪም ኤጀንሲው ከተመራማሪዎቹ ጋር በመሆን ለምርምር በተመረጡ ማሳዎች ላይ በመገኘት አርሶ አደሮቹ በሚቲዎሮሎጂ መረጃ አስፈላጊነትና በመረጃው አጠቃቀም ዙሪያ ጥልቀት ያለው ስልጠና እንዲያገኙ ከማድረግ ባሻገርም የግብርና ኤክስቴንሽን ባለሞያዎች እንዲሁም ለወረዳ ግብርና ባለሞያዎችና ኃላፊዎች ስልጠናውን ለብቻ እንዲያገኙ መደረጉንም ገልፀዋል፡፡

በፕሮጀክቱ አስፈላጊነትና አተገባበር ላይ በየደረጃው መግባባት ከተፈጠረ በኋላና ወደ ተግባር ከመግባቱ በፊት የደቡብ ክልል ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል የወቅት፣ የወሩን በሂደትም በየአሥር ቀኑና በየሶስት ቀኑ የተተነተኑ ትንበያዎችንና የምክር አገልግሎቶችን ለ25ቱ አርሶ አደሮች በስልክና በግብርናው መዋቅር በኩል ሲሰጥ መቆየቱም በተመራማሪዎቹ ተብራርቷል፡፡

በዚህ ጥናታቸውም የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ አገልግሎቶችን በቅርበት ያገኙ አርሶ አደሮች የምርት ዕድገታቸው በአማካይ በሄክታር ከአሥር ኩንታል በላይ መሆኑን አረጋግጠዋል፡፡





በዕለቱም ለምርምሩ እንደ መነሻ ሀሳብ የተወሰዱ ጉዳዮችንና የጥናቱን ግምገማ ውጤት ያቀረቡት ከሐዋሳ ዩኒቨርሲቲ ዶ/ር ደመላሽ ከፋለ ሲሆኑ ወረዳዎችንና አርሶ አደሮችን የመረጡበት መስፈርትና ለተመረጡት አርሶ አደሮች የተደረገውን ድጋፍ እንዲሁም ባደረጉት የምርምር ውጤት የተገኙ ውጤቶችን ከማስፋፋት አንፃር ያዘጋጁትን ዕቅድ ያቀረቡት ከደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ ከፍተኛ ባለሞያ አቶ ያረጋል አግደው መሆናቸውም ታውቋል፡፡

በተካሄደው ጥናትም ከሶስቱ ወረዳዎች ውስጥ በሸበዲኖ ወረዳ በተመረተው አደንጎሬ ላይ የምርት መጠኑ ኤክስፐርመንት በተካሄደበት ማሳ ላይ የቀነሰበትና ያለሚቲዎሮሎጂ መረጃ በዘሩ አርሶ አደሮች ምርታቸው በተቃራኒው የጨመረበት ሁኔታ የታየ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ለኤክስፐርመንታል ይሆናል ተብሎ የተመረጠውን ማሳ በቦታው ሲኬድ ማግኘት ያልተቻለበትና በታሰበው አካባቢም የተዘጋጀ መሬት ማግኘት ባለመቻሉ ምክንያት ሩቅ ቦታ አፋሩ ለአደንጎሬ ምርት ምቹ ባለመሆኑ፣ በጣም እርጥበት በበዛበት እና ውሃ በተኛበት ማሳ ላይ ለመዝራት በመገደዳችን ምክንያት ቀድመን ይህ ልዩነት ሊፈጠር እንደሚችል መገመታቸውና አማራጭ ስላልነበራቸው የተወሰደ ርምጃ መሆኑን ለተነሳው ጥያቄ ማብራሪያ ሰጥተዋል፣

የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎቶች አስቀድሞ ማግኘት የዝናቡን አገባብና አወጣጥ በማወቅ ለአርሶ አደሩ ምን ዓይነት ዘር መዝራት እንዳለበት ለመወሰን፣ ማሳውን ለማዘጋጀት፣ መቼ መዝራት እንዳለበት እንዲሁም መቼ ማዳበሪያ መጠቀም እንዳለበትና መቼ ምርቱን መሰብሰብ እንዳለበት ለማሳወቅ በአጠቃላይ ምርትና ምርታማነቱን ለማሳደግ ከፍተኛ ፋይዳ እንደሚያስገኝለት ተመራማሪዎቹ አብራርተዋል፡፡

ተመራማሪዎቹ በጥናታቸው ያመላከቱት ሌላ ጉዳይ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ኤጀንሲው የሚሰጣቸው መረጃ በአጨዳ ጊዜ ከሚሰጡ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያዎች በስተቀር ሌሎቹ በቂ አለመሆናቸውን ገልፀው በቀጣይ በመንግስታዊ መዋቅሮችና በዚህ ፕሮጀክት አተገባበር ላይ በስልክ እንዲሁም በኢሜይል እንደሚሰጠው ዓይነት የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች በኤጀንሲው የሚሰጥበት ሁኔታ ቢፈጠር የሚል ሀሳብ አንስተዋል፡፡

## በትግራይ ክልል ለሁለተኛ ጊዜ ተግባራዊ የተደረገው ፕሮጀክት የላቀ ውጤት የተመዘገበበት መሆኑ ተገለፃ፡

"በክልሉ ማህበረሰብ ዘንድ ያለው ግንዛቤ እያደገ ስለመጣ አሁን ላይ የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎት ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ብለን ከመጠየቅ ይልቅ ትኩረታችን በመረጃው ተደራሽነት ላይ መሆን አለበት"

*የግብርና ምርምር ተመራማሪ አቶ ተስፋዬ ገ/ፃድቃን፡፡*

ከታህሳስ 20-21 በትግራይ ክልል መቀሌ ከተማ አርሶ አደርን ጨምሮ ከ70 በላይ ተሳታፊዎች የተገኙበትን የምክክር መድረኩን በንግግር የከፈቱት አቶ ፈጠነ ተሾመ የብሔራዊ ሚቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተር ተሳታፊዎችን እንኳን ደህና መጣችሁ በማለት አገራችን የአየር ሁኔታና ጠባይ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ የተለያዩ አዎንታዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ላይ እንደምትገኝ በመግለፅ ለዚህም በአይሪሽ ኤይድ ፕሮጀክት የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን ተደራሽ ለማድረግ የተሰራው ሥራ በተለይም በዝናብ ላይ ጥገኛ ለሆነው ግብርናችን ምርታማነት እጅግ በጣም ወሳኝ መሆኑን ጠቅሰዋል፡፡

አቶ ፈጠነ በመቀጠል ኤጀንሲው የሚሰጣቸው አገልግሎቶች በአየር ሁኔታና ጠባይ መለዋወጥ ምክንያት በአገራችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ላይ ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት አስቀድሞ በሳማወቅ ጉዳቱን ለመቀነስም ሆነ ሀገራዊ ፕሮጀክቶችንና ፖሊሲዎችን ለመንደፍ በግብዓትነት የሚውል በመሆኑ ፋይዳው የጎላ ነው ብለዋል፡፡ የፕሮጀክቱ ዓላማም የክልሉ አርሶ አደር ዝናብ የሚገባበትንና የሚያበቃበትን ግዜ አስቀድሞ እንዲያገኝ በማድረግ የግብርና ምርታማነትን ለማሳደግ ታስቦ የተቀረፃ መሆኑንና በዚህም የተለያዩ ባለድርሻ አካላት መቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ የትግራይ ክልል ግብርና ቢሮ፣ የክልሉ ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው ተቋማት መሳተፋቸውን ገልፃዋል፡፡

ኤጀንሲው የትንበያና ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ የምክር አገልግሎቶችን ይበልጥ ተደራሽነት ለማድረግ እየሰራ መሆኑን ገልፃው በክልላችሁ የሚገኘው የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከሉም በዚህ ፕሮጀክት አገልግሎቱን ይበልጥ ተደራሽ እንዲሆን የተጀመረውን እንቅስቃሴና የተገኘውን ውጤት ይበልጥ አጠናክሮ ለማስቀጠል መስራት ላይ ትኩቱን ማድረግ እንዳለበት አሳስበዋል፡፡ በመጨረሻም ውይይቱ ውጤታማ እንዲሆን ያላቸውን ምኞት በመግለፅ የምክክር መድረኩ መከፈቱን አብስረዋል፡፡

በመጀመሪያ ለምርምር በተመረጡ በስምንት ወረዳዎች በተመረጡ የአርሶ አደር ማሳዎች ላይ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ የምክር አገልግሎትን ተደራሽነት ለማሳደግ የተከናወነውን

መነሻ የጥናት ውጤታቸውን ያቀረቡት በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ የአየር ጠባይና ማህበረሰብ መምህር የሆኑት አቶ አምዶም ገ/መድኅን ናቸው፡፡

የጥናት ውጤቱን የገመገመው ግብረሀይል የተውጣጣው ከመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣ ከክልሉ ግብርና ቢሮ፣ ከትግራይ ክልል ግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት እና ከመቀሌ ሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ማዕከል መሆኑና በዚህም ውስጥ የዘርፉ ተመራማሪዎችና ባለሞያዎች የተሳተፉበት እንደሆነም ከቀረበው ጥናታዊ ፅሁፍ ለመረዳት ችለናል፡፡





ጥናቱ የተካሄደው በመጠይቅና አርሶ አደሩን በቃል በመጠየቅ እንደሆነና በተዘጋጀው መጠይቅ ላይም ሁሉም የግብረ ሀይሉ አባል ከራሱ አንፃር እንዲያየውና በትክክል ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በሚያሳይ መልኩ መዘጋጀቱ ካረጋገጠ ብኋላ በ18 የግብርና ልማት ሠራተኞችና ከወረዳ በተመረጡ 12 የግብርና ባለሞያዎች እንዲሞላ መደረጉን፣ አርሶ አደሩንደግሞ በቃል በመጠየቅ በአጠቃላይ አርሶ አደሪን ጨምሮ አንድ መቶ የሚሆኑ በግብርና ዘርፍ የተሰማሩ ባለሞያዎች የተሳተፉና በእነዚህ መንገዶች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን የቀረበ የምርምር ውጤት መሆኑን ገልፃዋል፡፡

በትግራይ ክልል በአየር ሁኔታና በግብርና የሚቲዎሮሎጂ ምክር አገልግሎት አጠቃቀም ላይ በማተከር ሁለተኛ የምርምር ውጤታቸውን ያቀረቡት የክልሉ ግብርና ምርምር ኢኒስቲትዩት አቶ ተስፋዬ ገ/ፃዲቅ በጽሑፋቸው እንደገለፁት የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ለግብርናው እንቅስቃሴ ከማሳ ዝግጅት ጀምሮ እስከ አጨዳ ድረስ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ በጥናታቸውም የትግራይ ክልል ወቅቱን ላልጠበቀና የዝናብ እጥረት በብዛት የሚጋለጥ መሆኑንና በአጠቃላይ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴው ለአየር ሁኔታና ጠባይ ተፅዕኖ በጣም የተጋለጠ ስለሆነ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ እንኳን አስቸጋሪ የሚሆንበት ሁኔታ በስፋት የሚያጋጥም መሆኑን ጠቅሰው የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ለክልሉ ግብርና ውጤታማ መሆን እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ገልፃዋል፡፡ በዚህም ምክንያት በፕሮጀክቱ በተገኘው ድጋፍ ከኤጀንሲው ጋር በመሆን ለአርሶ አደሩ በቅርበት የተተነተኑ የአየር ሁኔታ መረጃዎችን ከመስጠታችን በፊት በአየር ሁኔታና ጠባይ መረጃ ፈይዳ እንዲሁም በመረጃው አጠቃቀም ዙሪያ ለአርሶ አደሩ ጥልቀት ያለው ስልጠና ለመስጠጥ ከፊተኛ ጥረት ተደርጎል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግብርና ኤክስቴንሽን ባለሞያ፣ ከክልል እስከ ወረዳ ግብርና ባለሞያዎች ድረስ ሁሉም በተናጥል በአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያ ፋይዳ ትርጉምና አጠቃቀም ዙሪያ በቂ ስልጠና እንዲያገኙ ከተደረገ በኋላ ወደ ተግባር መገባቱን ገልፃዋል፡፡ ስምንት ወረዳዎቹ የተመረጡት አግሮ-ኢኮሎጂያቸውን መሠረት በማድረግ ፣ ሁሉንም የአየር ጠባይ በሚወክል መልኩ የተመረጡ መሆናቸውን እንዲሁም በመጀመሪያ ዙር የአይሪሽ ኤይድ ፕሮጀክት ተግባራዊ የተደረገባቸው ወረዳዎች መሆናቸውን አስታውቀዋል፣

ለአርሶ አደሮቹ በኤጀንሲው በኩል የተሰጡትን የአየር ሁኔታና ጠባይ ትንበያዎች ተአማኒነት በተመለከተም በተጨባጭ መሬት ላይ ከተከሰተው አንፃር ያደረጉትን ግምገማ ሲያቀርቡ እንደመሆኒ የክርምት ዝናቡ በአገባቡም ሆነ በአወጣጡ የተሰጠውና የተከሰተውም ተመሳሳይ

መሆኑ፣ ክልታአውላሎም  እጅግ ተመሳሳይ መሆኑን፣ ገንታ አፈሾም አገባቡ ላይ የተሰጠውና በመሬት ላይ የተከሰተው ተመሳሳይ መሆኑንና ነገር ግን በአወጣጥ ላይ የተሰጠው ትንበያና የተከሰተው የተወሰነ ልዩነት የነበረው መሆኑን፣

በምርት ዕድገቱም ስናይ የምርት ዕድገት በገንታ አፈሾም =-13.3 qt/ha፣ ታህታይ ቃራሮ =+20.3 qt/ha፣ ክልታአውላሎ=+28.9 qt/ha፣ ራያ አዘቦ =+10.8 qt/ha፣ በአዲግራትና ኮራሮ ከመጀመሪያ ዙር የፕሮጀክት ትግበራ በላይ የጨመረበት ሁኔታ መታየቱን አብራርተዋል፡፡

ለሁለተኛ ግዜ ተግባራዊ በተደረገበት ወቅት ላይ አ/ፃንቢላ፣ ኢንደመሆኒ እና ውቅሮ የምርት እድገቱ በከፍተኛ ሁኔታ ጨምሮል፣ የምርት ልዩነቱ የተፈጠረው ምናልበትም በአፈር ለምነት ሊሆን ይችላል በሚል ባደረግነው የአፈር ምርመራም አፈሩ ተመሳሳይ መሆኑን ስላረጋገትን ልዩነቱ የመጣው በአየር ሁኔታ ትንበያ ምክንያት መሆኑን አረጋግጠናል፡፡

ከአይርላንድ መንግስት በተገኘው ድጋፍ ተግባራዊ ሲደረግ የቆየው ይህ ፕሮጀክት በክልሉ ለሁለተኛ ጊዜ የተተገበረ ሲሆን ይሄውም በ2006 ዓ.ም በፕሮጀክቱ የታቀፉ አምስት ወረዳዎች መሆኑና በ2009 ዓ.ም ደግሞ ሦስት ወረዳዎችን በመጨመር ወደ ስምንት ወረዳዎች እንዲያድጉ የተደረገ እንደሆነ ገልፃው የተመረጡ ወረዳዎች እንደየአየር ጠባያቸው መለያየታቸውን ማለትም ከወይናደጋ፣ ከደጋና ከቆላ በፕሮጀክቱ መታቀፋቸውንም ተመራማሪዎቹ ገልፀዋል፡፡

በክልሉ በተተገበረው መጀመሪያው ዙር አይሪሽ አይድ ፕሮጀክቱ ትግበራ ላይ ሰላሣ የአርሶ አደር ማሳ ለምርምር የተመረጠ መሆኑን፣ ከነዚህም ውስጥ በአሥራ አምስት የአርሶ አደር ማሳ ላይ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ የምክር አገልግሎትን ጨምሮ ሁሉም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓቶች የቀረቡ ሲሆን በቀሪው15 ደግሞ ከሚቲዎሮሎጂ ትንበያ በስተቀር ሁሉንም የግብርና ቴክኖሎጂዎች በ30ውም የአርሶ አደር ማሳዎች እንዲቀርቡ በማድረግ ሲሠራ እንደነበረና በሁለተኛው ዙር ደግሞ ሁለት መቶ የአርሶ አደር ማሳ የተመረጠ ሲሆን አንድ መቶ(100) የአርሶ አደር ማሳ ላይ የሚቲዎሮሎጂ ትንበያን ጨምሮ ሁሉንም የግብርና ምርት ማሳደጊያ ቴክኖሎጂዎች እንዲቀርቡ የተደረገ ሲሆን ቀሪው አንድ መቶ ማሳ ደግሞ የሚቲዎሎጂ አየር ሁኔታ ትንበያ ያልቀረበበትና ሎሎች የግብርና አቅርቦቶችን በተመሳሳይ በማቅረብ ሰፊ ጥናት የተካሄደበት መሆኑንም ተናግረዋል፡፡

ለአርሶ አደሩ በመጀመሪያ ዙር የተሰራጨው የዝናብ መጠን መለኪያ ሬንጌጅ 15 ብቻ ሲሆን በሁለኛው ዙር የፕሮጀክት ትግበራ ላይ ደግሞ ለ200 አርሶ አደር በማሠራጫት በአርሶ አደር ማሳ ውስጥ የተተከሉ መሆናቸውና በክልሉ አርሶ አደር ማሠልጠኛ ማዕከል ከተተከሉት ጋር 500 የሚሆኑ የዝናብ መጠን መለኪያ መሳሪያ (ሬንጌጅ) በክልሉ መሰራጨቱን እንዲሁም በመሣሪያው ጠቀሜታ፣ በመሣሪያው አተካከልና አጠቃቀም እንዲሁም ምን ያህል እርጥበት (ዝናብ) ሲገኝ አርሶ አደሩ ዘር መዝራት እንዳለበት ለአርሶ አደሩ ጥልቀት ያለው ስልጠና አስቀድሞ በመስጠት ወደ ሥራ መገባቱን ገልፃዋል፡፡ ከመቀሌ አገልግሎት ማዕከልም በየጊዜው የተተነተኑ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የምክር አገልግሎት ሲሰጥ መቆየቱና አርሶ አደሩ ደግሞ በማሳው ውስጥ በተተከለው የዝናብ መጠን መለኪያ መሣሪያ አማካኝነት የተመዘገበውን መረጃ ለኤጀንሲው ይሰጥ እንደነበረም አብራርተዋል፡፡

በፊት በብዛት አርሶ አደሩ በቂ እርጥበት አግኝተው እንኳን 3 ሳምንት ዘግይቶ የሚዘሩበት፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባሉ አርሶ አደሮች ደግሞ በቂ ርጥበት ሳይኖር የሚዘራበት ሁኔታ በስፋት የሚስተዋልበት ሁኔታ መኖሩንና በተሰራው የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች አሁን ላይ ግንዛቤው በከፍተኛ ሁኔታ እያደገ መምጣቱን እያየን ነው በማለት ጥናት አቅራቢው ገልፀዋል፡፡

በማጠቃለያ መድረኩ ላይ የተሳተፉት አርሶ አደሮች በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት በየደረጃው የሚገኙት የግብርና ባለሞያዎችና ተመራማሪዎች በየግዜው በማሳችን ላይ በመገኘት ድጋፍ ስላደረጉልንና ከምርጥ ዘር ጀምሮ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎችን በማቅረብ ጭምር ስለደገፉን ዛሬ ምርታችንን በከፍተኛ ደረጃ ማሳደግ ችለናል ብለዋል፡፡

ጥናት አቅራቢዎቹ የአርሶ አደሩ ግንዛቤ እያደገ በመምጣቱ አሁን ላይ የሚቲዎሮሎጂ አገልግሎት ይጠቅማል ወይስ አይጠቅምም ብለን የምንጠያየቅበት ጊዜ አለመሆኑን ይልቁንም በፕሮጀክቱ በጋራ የጀመርናቸውን ሥራዎች ወደ ሁሉም አርሶ አደሮች የማስፋቱ ሥራ ተጠናክሮ መሰራት እንዳለበት አንስተው ለዚህም ኤጀንሲው ማዕከሉን በማጠናከር በክልሉ ከሚገኙ ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር ተቀናጅቶ በየግዜው መረጃዎችን ማቅረብ የሚችልበትን ሁኔታ ለመፍጠር ትኩረት ሰጥቶ ሊሠራ እንደሚገባ ገልፃዋል፡፡

የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር በመድረኩ ላይ ሲናገሩ ማዕከሉ የተቋቋመው ለክልሉ በቅርበት አገልግሎት ለመስጠት እስከ ሆነ ድረስ አገልግሎት ፈላጊው ተቋሙ እስኪመጣ ድረስ መጠበቅ የለበትም መረጃውን አስቀድሞ ለውሳኔ ሰጪዎችና ለክልሉ ማህበረሰብ መረጃውን መስጠት ይኖርበታል፡፡

ተመራማሪዎቹ ከፕሮጀክቱ መጀመሪያ ጀምሮ እስከ መጨረሻው ድረስ ከኤጀንሲው ጋር ሆነው ለተገኘው ውጤት እንድንበቃ ስላደረጉን እጅግ በጣም ለመሰግናቸው እፈልጋለሁ ብለዋል፡፡

አቶ ፈጠነ በመቀጠል መረጃውን ተደራሽ ለማድረግም ከሚዲያ ተቋማት ጋር በተለይም ከድምፀ-ወያኔ ጋር ተቀናጅቶ መስራት እጅግ አስፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው ከምንም ነገር በላይ ግን ከዚህ ቀደም እንደ ሴክተር ተናቦና ተቀናጅቶ በጋራ ከመስራት አንፃር ከፍተኛ ክፍተት መኖሩንና ልምድም እንዳልነበረ የገለፁ ሲሆን በዚህ ፕሮጀክት ግን ሁሉም ባለድርሻ አካላት ተቀናጅቶ ተቀራርቦ በመሥራት በኩል ከፍተኛ ውጤት መገኘቱን በማሳያ ጭምር ለቤቱ አስረድተዋል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ አርሶ አደሩ የመረጃውን ጠቀሜታና በመጠቀሙ ያገኘውን ውጤት በዚህ ሁኔታ መግለፁ ከዚህ በላይ አስረጂ አያስፈልግም ብለዋል፡፡ በዚህ ፕሮጀክት የተገኙትን ተሞክሮዎች ወደ ሌላ አርሶ አደር በማስፋፋት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባ ገልፀው ለዚህም ሁላችንም የድርሻችንን ሚና ልንወጣ ይገባል በማለት አሳስበዋል፡፡